## ገጽ ፪

ማርያማዊትን እወዳት ነበር፤ ሕይወቴ ላይ አሻራዋ ጉልህ ነው። ምን ያላደረገችልኝ ነገር አለ? የከፋኝ ዕለት፣ ኪሴ ውስጥ ሳንቲም ያልነበረ ዕለት፣ አላዋቂነት የመሰከረብኝ ዕለት፣ ልብሴ እንደቸሰትኩ ያቃጠረብኝ ዕለት፣ የተንሻፈፈ ጫማ የተጫማሁ ዕለት አብራኝ ነበረች፣ የደመነብኝ ዕለት ሁሌ ከጎኔ አትለይም።

ሳንቲም ከኪሴ ሞልቶ፣ ባንኬ ላይ የጠቀጠቅኩኝ ወቅት፣ አለቃ የሆንኩ ዕለት፣ በእይታዬ አልያም በዕውቀቴ የተጨበጨበልኝ ቀን አብራኝ ነበረች። መጽሐፌ ሲታተም ምስጋናዬን ለእሷ ብቻ ሰጥቻለሁ፤ መመረቂያ ጽሑፌ ላይ በጉልህ የእሷ ስም ነው ያለው፤ እወዳታለሁ ስል ፍቅሬ የሚዳሰስ ነው።

ካደኝ ትላለች።

ስታገኘኝ ሱሴ እየበላኝ፣ እያደቀቀኝም ነበር። ለራሴ ያለኝ ስፍራ እዚህ ግባ የማይባል ነበር፤ ባንክ ቤት ስሄድ ወረፋ መያዣ መቀመጫ ወንበሩን የማቆሽሸው ያህል ለመቀመጥም የማልመጥን ነበር የሚመስለኝ። ሱሴ ልምጥምጥ አድርጎኝ ነበር፤ ተስፋ ያልቆረጠብኝ አንድም አልነበረም። ስለ ደቂቃ እና ሰዓታት እንጂ ስለ ነገ የማላስብ ነበርኩ። ማርያማዊት ነች ቁልቁል አይታ ያነሳችኝ።

ግን ካድኳት።





ታውቃለች እንደምወዳት፣ ታውቃለች እንደማከብራትም። ታውቃለች ላገኘሁት ሰው ሁሉ እንደማጣቅሳት። ያኔ ገና በንፁሕ ወዳጅነት እያለን አንስቶ ስትባትልልኝ ነው ውለታዋ ደምስሬ ውስጥ የሰረጸው። ከሁሉ ሰው በተለየ ስለምታየኝ፣ ስለምታዝንልኝ፣ የወዳጅነት ፍቅሯ፣ መላመዳችን ሲጨማመር በፍቅሯ ወደቅኩ።

አንድ ጊዜ አባቴ ታመመብኝ። ለአባቴ ከእኔ በቀር ማንም አልነበረውም። ሥራ ፍቃድ አላገኝ ስል የዓመት ፍቃድ ወስዳ ቀን ከሌሊት አባቴን አስታመመችልኝ። ለአባቴ መድኃኒት ለመግዛት ሲወደድባት እሱም የለውም ብላ የአንገት ጌጧን ሸጣ መድኃኒት መግዛቷን ያወቅኩት ወርቅሽ የት ሄደ ብዬ ስጠይቃት "ለአባባ መድኃኒት መግዣ ሳንቲም አልነበረኝም፤ አንተ ደግሞ ወጪ ላይ ስለነበርክ ከማስጨንቅህ ብዬ ነበር የሸጥኩት" በሚል መልሷ ነበር።

ፍቅርን ሳያንኮሻኩሽ የሚኖር የተባረከ ነው። ስጦታ ነፍስ ከማዳን በላይ ምን ያደርጋል ብላ ነው የሚሆነው።

ሌላ ቀን ስብሰብ ብለን እየጠጣን፣ እራት በልተን እንዳበቃን ጃኬት ኪሴ ውስጥ ገብታ ወጣች፤ ትንሽ ቆይታ "ስልክህ ቴክስት ገባልህ" አለችኝ ሳየው ራሷ ናት የላከችው። "ጆለሴ ኪስህ ውስጥ እኮ ብር አለ ክፈል እንጂ" ይላል። ቢል ሲመጣ ተሻምቼ ከፈልኩ። መክፈል ውስጥ ያለውን ሥነ-ልቦና ታውቀዋለች። ያለመክፈል ውስጣዊ ስሜት ቢገባት ነው። እንድተልቅላት ነው፤ እኔ ከምከፍል አንተ ክፈል፣ አንተ ስትተልቅ እኔ እተልቃለሁ ብላ ነው።



Scanned with CamScanner

በስንት ጣር እንቅስቃሴዬን አይታብኝ ስትጠይቀኝ ነው ፍቅሬን የገለጥኩላት። ተንጠራርቶ ማፍቀር ይቻል ይሆናል፤ ተንጠራርቶ ፍቅር መንገር ግን ቀላል አይደለም። በጣር ተቅለስልሼ ፍቅሬን ገለጽኩ፤ በቀን ብዛት እሺም እምቢም ሳትለኝ ራሳችንን ፍቅረኛሞች ሆነን አገኘነው። ጥንካሬዋን አጋባችብኝ፤ ድክመቴን ተጠግታ አተነነችው፤ አብረን የማንውልበት ጊዜ ጠፋ። እኔ ግን በመጨረሻ ካድኳት። ግን ለምን ካድኳት?!

ማርያማዊት ሱሰኛው ቶማስን፣ በራሱ የማይተማመነው ቶማስን፣ ልምጥምጡ ቶማስን ሱሱን አስትታ ልበ-ሙሉ አድርጋው ቆፍጥኖ እንኳን የትናንቱን ቶማስ ልትረሳው አልቻለችም። የተቀየርኩ ይመስላታል እንጂ እንደተቀየርኩ አልተቀበለችኝም።

ፈርጠም፣ ኮራ ብዬ ሳወራ ትገረማለች። እኔ ላይ ፈርጠም የሚል ፊት መሰስ እያለ ራሱን ይገልጣል። የዋለውን ውለታ ለዋሉለት በየሰበብ አስባቡ ማጣቀስ ውለታውን የማኮስመን አቅሙ ግዙፍ ነው። መልካም አድራጎት የሚገዝፈው መልካም አድራጊው በየሰበቡ ካልፎከረበት ነው። ትናንት ያ ኮስማና ቶማስ ማርያማዊት ላይ ተንጠልጥሎ ገዝፏል እና ሁሌ ተንጠልጥሎ ይኖራል?!

ማርያማዊት አታከተችኝ።

ከእሷ ውጪ መቆም እንደምችል በርካታ ጊዜ አሳየኋት፤ ማርያማዊት ተማሪዋ ነው የምመስላት። ስታየኝ፣ ሳወራት፣ ስንጫወወት ማረም ነው የሚታያት። ከእሷ ውጪ ተረማምጄ ማሳካት እንደሚቻለኝ በተደጋጋሚ አሳይቻታለሁ። አጥፍታ፣ ተሳስታ





ላሳያት ስሞክር እና አልሰማ ስትለኝ ፈርጠም ስል ማርያማዊት እኮ ነኝ ስማር እንኳን B የለኝም ዓይነት ሽለላ ትሽልላለች። የሰው ልጅ ስለሆነለት እና ስላገኘው ሁሌ የሚመሰጥ ፍጡር አለመሆኑ አልገባትም።

በየጊዜው "Never outshine the master" ዓይነት መልዕክት ታስተላልፋለች። አንድ ቀንም ስለ ጉብዝናዋ፣ ስለ ጥንቃቄዋ ተጠራጥሬ አላውቅም። ግን ጎበዝ መሆን ማለት ስሕተት አልባነት ነው እንዴ? ዘወትር አለቃህ ነኝ፣ የሕይወትህ መሥመር ቀያሽ እና አዳሽ ነኝ ከሚል ሰው ጋር መሆን ከበደኝ። ለማስተካከል ንግግር ስጀምር ትናንትህን ረስተሃል፤ ትናንትን ዞር ብለው ያላዩ ሰዎች ወሬ ልብህን አጠገበህ ትለኛለች።

አታከተችኝ!!!

ሳገኛት ለፈተና የተዘጋጀ፣ ኤክስ እንዳይገባበት የሚጠነቀቅ ተማሪ ዓይነት ስሜት ይሰማኛል። የተሰማኝን ነገር ላለማስተያየት ሞከርኩ፣ ግን አልቻልኩም። በተለያየ ጊዜ ስሜቴን፣ ፍቅርንም፣ ጭቅጭቅንም ተገን አድርጌ አብራራሁ፤ ላስረዳትም ሞከርኩ። የበላይነት ስሜቷ ውስጥ የተወሸቀ የበታችነት ስሜት አቀጥቁጦባታል። ወይ እንደ እሷ ሰው መቀየር አልችልም፤ አልያም እሷ እንደ እኔ ለመቀየር ዝግጁ አይደለችም፤ ብቻ አብሪያት መሆን ሲያታክተኝ መታከቴ ከአቅሜ በላይ ሲሆን ተውኳት!

እሷ ከሕደት አለችው።

## ገጽ ፲

ድሮስ በዳይ የሚለው ያጣል? ላገኘው ሰው ሁሉ ፍሬከርስኪ እንደሚዘበዝብ ነግረውኛል።

ልቡ የሸፈተን ሰውን ልብ ማሸነፍ ግዙፍ ድንጋይ ዳገት ላይ ይዞ ለመውጣት መሞከርን ያከላል። ቶማስ ሳጠፉ፣ ሳስቀይመው ወይም ሳናድደው ስለ ማስተካከል እያሰበ አይደለም የሚሞግተኝ፤ እንዴት ልለያት እያለ መለያያ መንገድ እያነፈነፈ ነበር። ጭንቅላቱ ከሃዲ፣ ውለታ ቢስ እንዳይለው ጣፋጭ መለያያ ምክንያት እያከማቸ ነው ከእኔ ጋር የነበረው።

ከበደሉ በጣም እንደው በጣም ያመመኝ እንደሚያዝንልኝ መዘብዘቡ ነው። ያደረገውን እያወቅን በዳይ፣ አዛኝ መስሎ ሲጎዘጎዝ ሳይሰቀጥጠው መስማት የሚቻለው ምን ዓይነት ጆሮ ነው!?

ዓለማችንን ያጎደፉት እየበደሉን ደግመው መጥተው ለበደላቸው ከአራምባ እና ቆቦ ምክንያት እየደረቱ የሚደረድሩ፤ ተጠቅመው ሳለ እንደተጎዱ ሙሾ የሚያወርዱ ተርመስማሽ ነፍሶች ናቸው።

ደግሞ የበደሉትን ስለሚያብለሰልሷት በደላቸውን ማፍዘዝ አሳማኝ የምትመስል ነገር አያጡም። ትናንት እኮ ሰዎች አብሮኝ ሲሆን ለሱሱ ሳንቲም እየለመነኝ እንጂ የልብ ወዳጄ አይመስላቸውም ነበር። ትናንት ከእሱ ጋር ስሆን የሚያየኝ ስንት ሰው አዝኖ





አይመጥንሽም እያለ መከሮኛል። ሐሳባቸውን የጫጫታ ያህል እንኳን ቦታ አልሰጠሁትም ነበር።

እሱ ግን ካደኝ!

አጣጥለው ሲያዋሩት፣ ሲቀልዱበት እና ሲያሳንሱት ከስንቱ ጋ ተሟገትኩ? ከስንቱ ተጣላሁ? ጭሎ አድርገውት እኩዮቹ ሲልኩት፤ ታናናሾቹ ሲያሳንሱት ስንት ቀን ቀና እንዲል ባተልኩ። ወደ በጎ መለወጥ ብዙ ጠመዝማዛ መንገድ አለው። እንደ መበላሸት ቀላል አይደለም። እሱን ለመለወጥ ስንት መጽሐፍ አነበብኩ? ስንት ስልጠና አስገባሁት? እሱን ለመቀየር ስንት ቀፋፊ ስፍራዎች ዋልኩ?

ከማይረባ ሰው ጋር ሆንሽ በሚል ቤተሰቦቼ መከሩኝ፣ ጨቀጨቁኝ፣ ተጣሉኝ። እኔ ግን ተጋፈጥኩ።

እሱ ካደኝ እንጂ!!

ሱስ አሸንፎት ምን ያልሸጠብኝ ነገር ነበር? ከቤተሰቦቼ የተቀበልኳቸው ስጦታዎች እጄ ላይ መቼ አሉና? መቀየሩ ስጦታዬ ይሆናል ብዬ ነበር የታገስኩት። ለምንፈልገው ነገር ዋጋ ካልከፈልን የምንፈልገውን ነገር መቼ እናገኛለን!

እሱ ግን ካደኝ!

ተነጫናጭ፣ ግትር ነሽ ይለኛል። ነገር ግን ያኔ ንፁሕ ወዳጆች ሳለን ጭምር አስቸጋሪነትሽ ለታገሰሽ ደቂቃዎች እንኳን አይከርምም ይለኝ አልነበር? ትናንት አሜን ያለውን ማንነቴን ዛሬ ጎረበጠኝ አለ።



Scanned with CamScanner

ይሄን ማንነቴን እያወቀ እና እያየ እኮ ነው ከመጠንኩሽ ፍቀረኛ ካልሆንን ያለኝ።

ዛሬ ከሱሱ ሲላቀቅ፣ ሲያምርበት፣ ጥሩ ደመወዝ ሲያገኝ፣ አሊቃ ሲሆን ትናንት በደከመበት ወራት የተቀበለው ማንነቴ ኮሰኮሰው።

ሕሊናው ሲጠይቀው፣ ሲሞግተው ያሳለፍናቸውን ጥልፍልፍ መንገዶች ለማያውቁ፣ ለማይሞግቱ ሰዎች ጥሩ ሰው ነች ግን ካድኳት ብሎ ጆሮ ሲሰጡት ኃጥያቴን አግዝፎ እና አለስልሶ ያትታል። የውስጥ እውነት በጭብጨባ ሆነ በእርግማን ብዛት የሚዛነፍ መስሎት። ኢየሱስን የከሰሱት እና የሰቀሉት እኮ ያልደረሰባቸው እና የፈወሳቸው ናቸው፤ ሰቃይ እና ከሳሾቹ ሲጠየቁ የሚሉት መች አጡ?

እሱ ግን ትዝታችን ይበቃኛል ያልኩትን አላመነኝም!...



# ባል-ተመኝሁ

አስተዳደጌ ነው የገደለኝ። አስተዳደጌ መጠበቅ እና ማግኘት ነበረበት። አባቴ ሁሌ ቃል ይገባልኛል፣ የሆነ ነገር በጥሩ መልኩ ሳደርግ ይሸልመኛል፣ እናቴ የቤት ሥራ ስሠራ ታመሰግነኛለች፣ ትመርቀኛለች። በምስጋና እና በስጦታ ተንበሽብሼ ነው ያደግኩት፤ ለዛ ነው የጠበቅኩትን ሳጣ የምታመመው ብዬ ሁላ አውቃለሁ፤ ግን በእሱ ብቻም አይደለም!

የማያቸው ሮማንቲክ ፊልሞች እና የማነባቸው መጻሕፍት ናቸው፤ ከፍቅር የሚገኘውን ደስታ እና ሁኔታ ከሚገባው በላይ አጋነው፣ ከቅዱስ የማገኘውን ነገር ሁሉ ያሳነሱብኝ ብዬም አምኜ አውቃለሁ።

ግን እሱ ብቻ አይደለም!

ቅዱስ ራሱ ነው ፍቅረኛሞች እያለን አባቴን መስሎ እና ሆኖ ተንከባክቦ ኑሮ ስንጀምር እርግፍ አድርጎ ትቶኝ የተፈላጊነት ስሜቴን የገደለው።

ኖ በእሱ ብቻም አይደለም!

ገመናዬን፣ ሚስጥሬን፣ ስሜቴን ለሰው ስለማልናገር ነው መፍትሔ ያጣሁት፤ የማይቀለኝ! የሚያብከነክነኝ!

ግን ዋናው ምክንያት ይሄም አይደለም!



Scanned with CamScanner

ራሴን ከዋናው የሕመሜ ምክንያት፣ የድባቴዬን ምንጭ ለራሴ አልነግር ብዬ ነው።

ቅዱስ አይፈልገኝም። ሲመጣ ባዶ ቤት ቢቆየው ቅር አይለውም። ለስሜቴ ደንታ የለውም። ቆይ ስንት ወራቶች ሞላን ወሲብ እንኳን ከፈጸምን? አልጋ ከለየን ስንት ጊዜ ሆነን? ስንቴ ተዘገጃጅቼ ሊወጣ ሲል፣ ሲገባም ላነሳሳው በሚል አጋጣሚ አስመስዬ ራቁቴን የታየሁት፣ ቀስቃሽ አለባበስ ስንቴ ነው የለበስኩት?

እሱ ግን አያየኝም።

እንዲያዝንልኝ ታመምኩ፤ ኡኡ ነደድኩ፣ ጠዘጠዘኝ፣ ወጋኝ አልኩ፤ ታከሚ ይላል እንጂ አይደነግጥም። ወጣ ብሎ ስልክ ረጅም ሰዓት ያወራል።

መሀላችን ያለው ችግር ቀላል ነው ብዬ አስመሰልኩ... እውነቱ ግን እሱ አይወደኝም።

በመጨረሻ አልፈለግነት ሲጫወትብኝ፣ የድሮ ቦይፍሬንዴ ጋ ሄጄ ተልከሰከስኩ!

እሰይ!! እንኳን ተልከሰከስኩ።

ለሴት ልጅ የአለመፈለግነት ስሜት፣ ለዛውም በእንክብካቤ ላደገች፤ ለዛውም ተለማምጦ፣ ልዕልቴ ናት ብሎ ላገባት፣ ለዛውም መፈለግ እና መውደድ ለምታውቅ ሴት የሚሰማትን የሕመም ስሜት የት ያውቀዋል?!

የምን ጉዝጓዝ፣ ሰበብ፣ ድሪቶ፣ ዝባዝንኬ ነው?!





አለ'መፈለግ ብቻውን ቀላል ነው?!

ብቻውን ትዳርን መፍታት ብቻ አማራጭ አድርጎ ማሰብ ቀላል ነው?!

ብቻውን ወሲብ ማድረግ መፈለግ እና ባል እያለ በፍትወት መቸንከር ቀላል ነው?!

ብቻውን ላወራው እየፈለግኩ፣ ስደውልለት ሳያነሳልኝ ሲቀር አያከብረኝም፣ ከምንም አይቆጥረኝም ዓይነት ስሜትስ ቀላል ነው?!

ብቻውን እንዲህ አለዋለሁ ብዬ የሰበሰብኩትን ዓረፍተ ነገር፣ እንዲያዝንልኝ ያጠናሁትን ንግግር፣ እንዲታረቀኝ ያጠራቀምኩትን ቃላት፣ እንዲሳሳልኝ ያከማቸሁትን ሰበብ፣ እንዲረዳኝ የተዘጋጀሁበትን ቃል ፊት ነስቶ ሲያጠፋብኝ ስሜቱ ልብ አይሰብርም??!

ከድሮ ቦይፍሬንዴ ጋር ተንገብግበን፣ ተጠማጥመን ተዋሰብን። ቆንጆ ነኝ ወይ ስለው "ከድሮ በበለጠ" እያለኝ፤ ምኔን ትወድልኛለህ ስለው እያንዳንዱ አካሌን እየሳመ እያሳየኝ። እየተዟዟርን፣ ቦታ እያማረጥን ተዋሰብን።

ደስስስ አለኝ!!

ለመለምኩ! እየጠወለግኩኝ ነበር።

ያደረግኩት ተግባር ለሌላው፣ ለመንገደኛው፣ ለመርሕ ሰው ሁሉ፣ ለጨዋው ሁሉ፣ ለአማኙ ሁሉ፣ ከዳር ሆኖ ላየኝ ሁሉ፣ ለፈራጅ ሁሉ፣ ለሌባው ሳይቀር ዝሙት ነው!

ወሲብ ውስጥ ያለውን እፈልግሻለሁ፣ ታምሪያለሽ፣ እወድሻለሁ ሽንገላን መስማት ናፍቆኝ ነበር።



Scanned with CamScanner

አመሰግንሃለሁ ብዬ አንገቱ ውስጥ ተወሸቁ ሳምኩት። ስለተኛኸኝ አመሰግናለሁ ይባላል? ትዳሬ ላይ ከባለግኩኝ በኋላ ማመስገን ነበረብኝ?

እኔ ግን አመሰገንኩት!

ተሰናብቼው ሳይመሽብኝ ወደ ቤቴ ፈጠን ፈጠን እያልኩ መሄድ ጀመርኩ፤ ቀስ እያልኩ ፍጥነቴን ቀነስኩ፤ እዛ ዱካክ፣ አልፈለግነት የሚበላኝ ቤት መሄድ ፈራሁ። የማይፈልገኝን ባሌን ማየት ሲያልን የማየት ዓይነት ሆነብኝ፣ የማይናፍቀኝን፣ የማይንከባከበኝ ባሌ ያለበት ቤት መሄድ ጠላሁ፣ ወስልቼበት እንኳን ጸጸት ያልተሰማኝ ባሌ ጋ መሄድ አስጠላኝ።

ለመጀመርያ ጊዜ ልቤን ሰማሁት።

ከእኔ ካልሆነ ሰው ጋር አንድተኛ ያደረገኝ ሰውዬ ጋ ምን አደርጋለሁ??

መሳም እስክናፍቅ ድረስ የገፋኝን፣ መታቀፍን ብርቅ ያደረገብኝን፣ መወደድ እንደሚገባኝ ያስረሳኝ ሰው ጋ ምን አደርጋለሁ?!

ምን አጠፋሁ? ይቅርታ ለማለት፣ ምን ላድርግልህ እንድለው ትንሽዬ እንኳን ፊት የማይሰጠኝ ሰው ጋ ለመኖር ለምን እሄዳለሁ?

ወደ ኋላ ተ መ ለ ስ ኩ።



# ሊያብብ ሲል

ሱስ ሳይበላው፣ ሲጋራ መግዣ መለመን ሳይጀምር፤ ጉስቁልና ሳያፈዘው፤ ለልብሱ መቆሸሸ ደንታ ቢስ ከመሆኑ በፊት፤ ሰዎችም ሲጣራ ባልሰማ መሄድ ሳይጀምሩ፤ ቃል አባይ ከመሆኑ በፊት፤ ክብሬ ማለት ሳያቆም፤ ለትንሽ ለትልቁ መላክ ሳይጀምር በፊት... ቆንጆ፣ ተወዳጅ፣ ዘናጭ ነበር። ከጓደኞቹ በላይ ድምቅ ያለ ልጅ ነበር፤ ቆንጆ አማርጦ ይሰክስ ነበር፤ የጸጉሩን ፍሪዝ በመሰታወት አስር ጊዜ እያየ አስር ጊዜ ያስተካክል ነበር።

ሕልመኛ ነበር። እንደ ሁሉም ወጣት ሀብታም መሆን፤ አዋቂ መሆን፤ ቤተሰቦቹን የመርዳት ሕልም ነበረው። የተንሸዋረረ አራድነት አሳስቶት የለኮሳት ሲጋራ፤ ለሳቅ ብሎ የተጎነጨት አረቄ፣ ለሙድ ብሎ የቀነጠሳት የጫት ቅጠል ስትደጋገም አፈዘዘችው፤ ሕልሙን ወጣትነቱን ክብሩን አረገፈችው።

ማንም ብርቱ ነኝ ቢል ታግሎ የማያስመልሳትን ወጣትነቱን ለማያቀው ጣያት እየሰዋት ነው።

ጥግ ላይ ተቀምጦ ዘመን ሂዶ ዘመን በመጣ ቁጥር የሚመጡ ለውጦችን ከዳር በትዝብት እየተመለከተ 'ጊዜው እንዴት ነው የሚሮጠው?' የሚል ይመስለኛል።



Scanned with CamScanner

# ምሶሶ እና ማገር

ሽክሜን ሳላስተያየው፣ ፍላጎቴን ቸል እያልኩ ከኔ በቀር ማን አለው ለምለው ቤተሰቤ ስል ፍላቴን አቀዝቅዤ መናገር የምፈለገውን ሁሉ ሳልናገር እንደ ጓደኞቼ ፋሽን ልከተል ሳልል ኑሮን ለማሸነፍ ስለምባትል ...

የቤታችን ምሶሶ እኔ ነኝ ባይ ነበረኩ!!

ድንገት እናቴ በአስር ቀን ሕመም ተለየችን። ቤታችን በፍጥነት ቀዘቀዘ።

እናታችን የአባቴን ስኳር፣ ደምብዛት እና ኮሌስትሮሉን ያማከለ ምግብ አቀናብራ አቅራቢ ነበረች። ተኝቶ ሳለ ከውጪ ሆነ ከቤት ውስጥ የሚረብሽ የመሰላት ድምጽ ከተተነፈሰ 'ቀስስ ቀስ ገረመው ተኝቷል' ትላለች ድምጿን ለምልክት በቀረበ ማንሻካሾክ። አባታችንም እንዳይረበሽ ድምጽ ቀንስ ለምትለውም ሰው እንዳይቀየም እየተጨነቀች። አባታችን እናታችን ከሌለች ቤት ውስጥ ያገኘውን ሰው 'አልሚ የት ሄዳ ነው? በቃ አንዴ ከወጣች አትመለስም?' እያለ በስሱ ይነጫነጫል። ምቾቱ ሲሰወርበት ማን ዝም ይላል?

የታናሽ ወንድሜ ሱስ ያመጣበትን ግትልትል ብልግና የምትደበቅለት፣ የምትሸሸግልት፣ ብላ እንጂ ገንዘብ የለህ እንደው አንዱ ቦታ ገባ ብለህ የምትጎርስበት፤ እነዛ ጓደኞች እንደሆኑ ሊያጠጡህ ነው የሚፈልጉህ... ደግሞ ሰውነትህ እየቀነሰ ነው... ወይ





እንደ ጎረምሳ ጎረስ ጎረስ አድርገህ አትበላ፣ በየትኛው አንጀትህ መጠጡን እንደምትችለው... እያለች ሳትሰለች ግሳጼ እና ምክር እያቀላቀለች ትኩረቷን የማትነግፈው፣ የምትቆረቆርለት፣ ከብልግናው መሀል መልካምነትን አነፍንፋ የምትመሰክርለት እሷ ብቻ ናት።

"ምዕራፌ እኛን እኛን እያልሽ ራስሽን አየበደልሽ እኮ ነው። ጸጉርሽን ተሰሪ እንጂ ደግሞ አማረልኝ እያልሽ ትጎምጂው እና ትጣይኛለሽ! ሴት ልጅ ጸጉሯ ነው ውበቷ..."

ውጪ ስትንገላታ ነው የምትውለው እያለች ታቀብጠኛለች፣ ትመከረኛለች፣ ገመናዬን ትሰማኛለች፣ ትገስጸኛለች፣ ጠዋት ማታ መግባት እና መውጣቴን፣ ሁኔታዬን፣ ገጼን፣ እንቅስቃሴን ትከታተላለች።

አደራህን ጌታዬ ከልጆቼ በፊት አድረገኝ፣ የልጅ ሐዘን አታሳየኝ፤ ከጓደኛ በታች አታውላቸው፣ ከከፉ ነገር ጋርዳቸው፤ ለኔ ያደረከውን ለማን አደረክ? ተመስገን፤ ተመስገን አያለች ስታጉተመትም ለሚሰማት ከአምላኳ ጋር የምታወራ አትመስልም፤ ከወዳጇ ጋር እንጂ!! በርግጥ ለታመነ ካምላክ በላይ ወዳጅ ማን አለ!

ምዕራፌ በርቺልን፣ ካላንቺ ማን አለን? እያለች መኖርያ ምክንያት ትለግሰኛለች። ለመመረቅ ሽራፊ ምክንያት የምትፈልግ ይመስል ላደረኩት ትንሽ ነገር ስትመርቀኝ ትውላለች።

ለውሻችን ቦቸራ እንኳን በሰዓቱ ምግብ የምትወረውርለት፤ አሞታል እንዴ? ፈዘዘሳ ብላ የምታስተውለው እናቴ ብቻ ናት።



Scanned with CamScanner

ዘመዶቻችን እንዲመጡ ወትዋች፣ ጠፋችሁ ብላ ወቃሽ፤ ሲመጡ ተንከባካቢ፤ ካልበላችሁ፣ ካልጨመራችሁ፣ ካልቆያችሁ፣ ካላደራችሁ እያለች የምትለማመጥ፤ ሰፈራችን ውስጥ ለቅሶ ሲኖር፣ ሰርግ ሲሰረግ፣ ዝክር ሲዘከር ግንባር ቀደም አጋዥና አድማቂ እናታችን ናት። ለሚውል መዋል፣ ለደግ ደግ መሆን ስለማይከብድ ቤታችን ጉዳይ ሲኖር የሚያግዘን፣ ስንታመም የሚጠይቀን፣ መንገድ ላይ ሰላምተኛችን ብዙ ነው።

ስናጣት ልካችን ተገለጠልን!! እንዴት ይሄን ሁሉ ስትሸከም በዚህ መጠን አላስተዋልኳትም? ተሸከሞ ሸክምን አለማሳየት ምን ዓይነት ጥበብ ነው?? እናቴን ያሳረፍኳት መስሎኝ ነበር፤ ለካ አሳርፋኝ ነው።

እናቴ ስንት ቀን ፍቅሯ እውነቷን ሲያስደብቃት፤ በድዬ ለእኔ ስታደላ አይቻታለሁ። ልጅ ሳለሁ በንዴት ከገረፈችኝ በኋላ ሲቃ እየተናነቀኝ ጉያዋ ስወሸቅ፣ ተንሰፍስፋ ያባበለችኝ ዕለት ትውስታ ልቤ ውስጥ አለ።

ድከመቴን የማታጎላብኝ፤ መውደዷ የማይወላውል፣ እንደምወዳት ማስረጃ የማታስስ፣ ተዝረክርኬ ዝንጥ እንዳልኩ የምታሰማኝ፤ ሕመሜ የሚያማት፤ ስኬቴ ከሁሉ በላይ የሚያስፈነድቃት፣ ነገሬን ሁሉ ጉዳዬ ነው የምትል፤ እንደምወደድ አስትንፋሴ ዓለም ላይ ካረፈ ጀምሮ እያሳየች የመሰከረችልኝ። አምወደድ እንደሆንኩ ልቤ ላይ ያሰረጸችልኝ፤ መወደድን የሚያክል ምንም በረከት እንደሌለ በምርቃት እና በጸሎቷ ያሰማችኝ።





ጥንካሬዋን ፈተና የማይበግረው፣ በደል ሆነ መከፋት የማይሸረሽረው፤ ትሕትና የተላበሰች፣ በየቀኑ ስለ ልጇ ከአምላኳ ጋ የምታወራ አመስጋኝ፣ ስጉ ፍጥረት ናት። እስከንጠግብ የማይርባት፤ አሟት በድካም የምታሳብብ፤ እየረገመችን የምትጸልይልን፣ አንደበቷ ከእውነቷ ጋ የማይገጣጠም ድብቅ ፍጡር ናት። ፍላጎቷን አሸሻ፣ የምትፈልገውን አጣጥላ ለምንወድው ነገር ፍላጎቷን የሰዋች፣ ለልጆቿ ቸር፣ ለራሷ ስስታም ናት።

የልጇን ፊት እንደ ዳዊት ዘወትር የምታነብ፤ ስትናፍቅ፣ ስናረፍድ በስጋት የምትቃዥ እናት፤ የፍጡር ፍቅር ጥግ ናት።

ዋርካችን ሲገነደስ የከለለልን ገበና ገለጠን!

ሞቷ ከእንባ በላይ ነው። አልቅሼ ላውጣው ብል አይወጣም። አንዳንድ ጊዜ አጠገቤ ያለች ይመስለኛል፤ ባትመልስልኝም የልቤን እንዲህ እያልኩ አወራታለሁ።

ለምን የሚወዱሽ ሲያለቅሱ፣ ደረታቸው ሲደቁ፣ ጸጉራቸውን ሲነጩ ዝም ብዬ ፈዝዤ ተመለከትኳቸው? አቅፈውኝ፣ አዝነውልኝ፣ እያለቀሱ ሲያባብሉኝ ለምን ደነዘዝኩኝ?

ግድ የለም አብሬሽ ሞቼ ነው የሚሆነው። አብሬሽ ሞቼ ባይሆን ድንኳኑ ውስጥ ወዳጅ አዝማድ ተሰብስቦ ሲጨዋወት፣ ሲያጽናና እኔ ለምን ብቻዬን ዲዳ ሆንኩኝ?

አብሬሽ ሞቼ ባይሆን



Scanned with CamScanner

የሚቀርበኝ ጉድሽ ፈላ እያለ ሲመለከተኝ፤ በርቺ አይዞሽ እያለ ማጽናኛ የቃላት ጋጋታ ሲያንጋጋ እንዴት በዚህ ሁሉ መሀል የእንባ ቋቴ አልተረታም? ከሩቅ፣ ከቅርብ ቀዬ ሐዘኔን በአካል ሊጋሩኝ መጥተው አይኔን እያዩ ሲያጨዋውቱኝ፤ ሊያበረቱኝ ሲታገሉ እንዴት ሆድ አይብሰኝም?

አብሬሽ ሞቼ ባይሆን

ቆሌ፣ ቅስሜ፣ ደመነፍሴ፣ ትውስታዬ፣ መጓጓቴ፣ ሕልሜ አብሮ ከአንቺ ጋ ባይቀበር እንዳሁኑ መች እሆን ነበር?

ከዚህ በኋላ አለመኖርሽ አንዴት አያባባኝም?

አንቺ ሞተሽ እኔ አብሬሽ ሞቼ ባይሆን አንድ ዘለላ እንባ እንዴት አልወጣኝም?

ይሁን ሁሉም... አብሬሽ ሞቼ ባይሆን ለምን ምሳዬ አይርበኝም? እንደሁሌው ውሃ ጥሜ ለምን አይታወቀኝም? ቆይ እሺ ለምን አትናፍቂኝም? አብሬሽ ሞቼ ባይሆን፣ ዋርካዬ ሲገነደስ እንዴት ዝም እላለሁ?

ነገሩ ምሰሶው ሲወድቅ ነው ማገር ማንነቱን የሚያውቀው!

# ከሳሽን መሰክርልኝ ይሉታል?

አለሌ ነበርኩ፤ ከሕንድ እስከ እብድ የቀረኝ የለም የምል አለሌ! የተኛኋቸው ሴቶች ጠቢቡ ሰለሞን ከተኛቸው የሚያንስ አይደለም፤ አልቆጠርኳቸውም እንጂ።

ጀንጅኜ መዳረሻዬ ማራኪ ሆቴል ነው። ሆቴሏ ከመኖሪያዬ ራቅ ያለች ሸጎጥ ያለ ሰዋራ ስፍራ ላይ የምትገኝ ነች። አስተናጋጆቹም ምቹ ናቸው። በእርግጥ ጉርሻ ምቹ የማያደርገው የለም። ፈረንጁ እና መስኪ የሚባሉ አስተናጋጆችን የበለጠ አውቃቸዋለሁ፤ ጠብ እርግፍ ብለው ያስተናግዱኛል።

መስኪ የምትባለው አስተናጋጅ ትንሽ ተለቅ ትላለች። ፊት ከሰጠሁት ይጎነትለኛል ብላ ይሆን፣ ተፈጥሮዋ ሆኖ ይሆን፣ ብዙ ሴት ስለማመላልስ ይሆን፣ ስለማጨስ ወይም ስለምጠጣ ይሆን እኔ'ንጃ ብቻ አትስቅልኝም አትኮሳተርብኝምም። ፊቷ ወጣትነትን ቢሸኝም ውበቷ ግን እንዳለ ነው፤ ምንም ያህል ቲፕ ብሰጣት አመሰጋገኗ ሆነ አስተያየቷ አይለይም፤ ተመሳሳይ ነው።

ከላሴ ውስጥ አጭሼ፣ ጠጥቼ፣ ባልጌ ሹልከ ብዬ በጓሮ እሄዳለሁ። በሌላ ቀን ሌላ ሴት ይዤ እመጣለሁ። ካልጠረረብኝ ሴት አልደግምም። ሁሉንም እንደ ሙዳቸው እና እንደ ፍላጎታቸው እሰከሳቸዋለሁ። ላጤነቴ በነጻነት ታየሁ አልታየሁ ብዬ ሳልሳቀቅ ለመባለግ አግዞኛል።

ጓደኞቼ ሁሉ ሲያገቡ፣ የቤተሰቦቼ የአታገባም ውትወታ በበረታ ወቅት ሶልያና የምትባል ልጅ ተዋወቅሁ። ባገኘኋት በሁለተኛው ቀን ይዣት ለመተኛት በት በት አልኩ፣ ግን አልተሳካልኝም። በውስጤ ስንቷ እንደ አንቺ አካብዳ ጭኗን ሳትከፍት የቀረች የለችም ብዬ ፈገግ ስል

"ምነው?" አለቺኝ።

እርጋታሽ ደስ ይላል

"ውስጤ እንደ ላዬ የተረጋጋ እንዳይመስልህ"

ይሆናል ግን፣ ውስጥም ላይም አንድ ላይ ከመንቀዥቀዥ ይሻላል ስላት

ከንፈሯን ገለጥ አድርጋ ሳቅኩኝ ዓይነት ፈገግ አለችልኝና

"በነገራችን ላይ አንተም ረጋ ያልክ ነህ"

ትዝብት ፈገግ ስልባት

"ውስጥህ ወዲህ ወዲያ ስለሚል ነው እርጋታህ ያልታወቀህ"

ይሆናል

ሶልያና የበዛ እርጋታ አላት። እርጋታዋ ይረብሸኛል። ከደስታ ይልቅ ለድብርት አጋልጦ ነው የሚሰጠኝ።

አብሪያት የምሆነው እስከወሰባት ድረስ ብቻ ነበር። መስማት ትፈልጋለች ብዬ የማስበውን እነግራታለሁ፣ ሲኒማ እጋብዛታለሁ፣ ትያትር ትጋብዘኛለች፣ ከንፈሯ ጋ ሳልደርስ ቀናቶች ነጎዱ።



የወሲብ ወሬ ለማውራት በጭራሽ አትመችም፤ ወሲብ ነክ ከተወራ ለመቀጠል ፊቷ አይጋብዝም፤ ወሲብ ነክ ቀልድ ባወራ ራሱ ለይሉኝታ እንኳን ፈገግ አትልም። መንፈሳዊ ጉባኤዎች ትጋብዘኛለች፤ ለእሷ ደስ እንዲላት አንዳንድ አስልቼ፣ አንዳንድ ማራኪ ስብከቶችን እሰማለሁ። ቀልቧን ለመግዛትም መንፈሳዊ መጽሐፍ እያነበብኩ፤ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ዕውቀት አለኝ ዓይነት ወሬ ሳወራት ቀልቧ ሲሳብ፣ ወሬው ሲጥማት አያለሁ።

ሳይታወቀኝ የኔን መንገድ እየተውኩ በእሷ መንገድ መመላለስ ቀጠልኩ። ከሌሎች ስለተለየች ይሆን፣ እንደምፈልገው አለመሆኗ ይሆን፣ የምፈልገውን ስላልሰጠችኝ ይሆን ብቻ ቀልቤን ገዝታዋለች። አዋዋሏን ሥራዬ ብዬ እከታተላለሁ፤ ካልተደዋወልን ይታወቀኛል፤ እንቅስቃሴዋ እየገቡኝ መጡ፤ ሳላገኛት የት እና ምን እያረገች እንደሆነ መገመት ቻልኩ፤ ከደወለችልኝ ስግብግብ ብዬ አነሳለሁ፤ በሂደት መንገዷ ምቾት ሰጠኝ፤ ከተመላለስኩበት መንገድ በተሻለ ይሄኛው መንገድ ጣፈጠኝ። ሶልያና ወሲብ የአካል ልፊያ ሳይሆን የነፍስ ውሕድት እንደሆነ አሳይታኛለች፤ ወሲብ ከፍቅር ውጪ ያልተቆራኘ አድራጎት እንዳልነበር ገባኝ፤ ሳላቀው መርኋን ኮረጅኩ፤ ኑሮ ከበፊት በተለየ ጣፈጠኝ።

የድሮ አመሌ ውል ሲለኝ፣ ይዣቸው የምተኛቸው ሴቶች ውልብ ብዬባቸው ሲደውሉ ሳላቅማማ የድሮ ስልክ ቁጥሬን ቀየርኩ። የትላንት የውድቀት መንገዳችንን ካልቀየርነው ለለውጣችን ሳንካ ይሆናል።

አሁን ፈልጌ መጽሐፍ ቅዱስ አነባለሁ፣ እጸማለሁ፣ ጉባኤ እከታተላለሁ፣ ቤተክርስቲያን እሄዳለሁ፣ ከሶልያና ጋ እንፋቀራለን። የትናንት መንገዴን አልተረኩላትም። ለዛሬው ማንነቴ ግን መሀንዲሷ እሷ ናት። ለአምላኬ ስንቴ በእሷ ምክንያት ምስጋና እንዳቀረብኩለት፤ የትናንት ሕይወቴን እንዴት አሁን እንደማልወደው፤ ስለ ሴት አውልነት ሲነሳ ምንም ሐሳብ አልሰጥም።

ያ ዘመን ያሳፍረኛል።

ሶልያና አንድ ዕለት ስትፍነከነክ መጣች። የደስታዋን ምንጭ ስጠይቃት

"እቴቴ ሥራ አገኘች"

የት

"ባንክ"

በቀላሉ ፍንክንክ የምትል አይደለችም፤ የእናቷ ጉዳይ ግን ስስ ጎኗ ነው፤ ብቻዋን ስላሳደገቻት ይሆን፣ እናት እና ጓደኛዋ ስለሆነች ይሆን፣ ብቻ ስፍስፍ ትልላታለች።

እናቷ ምን እንደምትሠራ አላውቅም ነበር። በትምህርት ያልገፋች ስለሆነች ማጽዳት፣ መላላክ ይሆናል ብዬ ገምቼ ምንድን ነው የምትሠራው፣ የት ነው የምትሠራው ብዬ ጠይቄያት አላውቅም። እሷም ሥራ ነች አልመጣችም፣ ሥራ ቀረች ነው እንጂ የት እና ምን እንደምትሠራ ነግራኝ አታውቅም። በረባው ባልረባው ወሬዎቿ መሀል





እቴት ሳትል አትውልም። የድሮ ሥራዋስ ስላት፤ "ውይ የድሮ ሥራዋን እኮ አትወደውም ግድ ሆኖባት እንጂ" አለችኝ።

ስለ እኔ እንደ ነገረቻት እና እንደ ወደደችኝ የነገረችኝ ዕለት እንዴት ደስ እንዳለኝ። የምንወደው ሰው በሚወደው ሰው ከመወደድ በላይ ምን ደስታ አለ? ባሻዬ ብላ ቴክስት አደረገችልኝ። (ደስ ስላት እና ስትቀልድ ባሻዬ ነው የምትለኝ)

"ከእቴት ጋ እንደምንመሳሰል ነግሬህ አውቃለሁ አ?"

ሁሌ ብዬ የሳቅ ስቲከር ላኩላት።

"እንደ እሷ ቆንጆ ነኝ ግን?" ብላ ፎቶዋን ላከችልኝ። ያየሁትን ማመን አልቻልኩም። ክው! ድርቅ አልኩ፤ የላከችልኝን ፎቶ አገላብጬ አየሁት፤ አልቀየር አለ።

የማራኪ ሆቴል አስተናጋጇ መስኪ የሶልያና እናት ናት። ሁለቱ አብረው ሆነው እና አንድ የመስኪን ማራኪ እንግዳ መቀበያ ጋ የተነሳችውን ፎቶ ላከችልኝ። ውስጤ ታወከ፤ ያ ሴት አውል አብርሃም፤ ያ በየጊዜው ቁጥር ስፍር ከሌላቸው ሴቶች ጋ የሚጋድመው፣ ሱሰኛው አብርሃም፤ ያ በጥሩ አይን አይታው የማታውቀው አብርሃም የአንድ ልጇ ሶልያና እጮኛ ነኝ ብሎ ፊቷ እንዴት ይቆማል??

ትናንቴ ተከተለኝ፤ እግዜር በተጸጸትንበት ትናንታችን ይቀጣናል እንዴ? ስንቴ ያመሰገንኩበት ጉዳይ መጨረሻው እንዴት እንደዚህ ሆነ??

አንዳንድ ትናንት ትናንት ላይ ብቻ አይቆምም። ዛሬያችንን የፈለገ ከትናንት አርቀን ስቅለነዋል ብንል እንኳን፣ ጥለነው ብዙ መጥተናል ያልነው ትናንት ነጋችን ላይ በሁለት እግሩ ቆሞ እናገኘዋለን።

በነዚያ ሁሉ የአለሌነት ዘመኖቼ ከእኔ እኩል ዘልዛላነቴን ቆማ የታዘበች እናት ፊት ከልጇ ጎን ቆሞ መታየት አቃተኝ። የማደርገው ጠፋኝ! ጠፋሁ። የሆነውን ሁሉ የማስረዳበት ቋንቋ ስላላገኘሁ ምንም ሳልላት ጠፋሁ።

ብዙ ሙብከንከን እና ድብርት የተሸከመ ቀን እያለፈ እንዳለ አንድ ተሾመ የሚባል በደንብ የሚያውቀን የጋራ ወዳጃችን ከብዙ ጊዜ በኋላ አግኝቼው፣ ከብዙ ጨዋታ በኋላ ከሶልያና ጋ ስላንተ አንስተን ተጨዋውተን ነበር ሲለኝ ሰፍ ብዬ ምን አወራችሁ አልኩት። ከዲያሪዋ ላይ ፎቶ አንስታ የላከችለትን ምስል ከሞባይሉ እንዳነበው ሰጠኝ።

"አብርሃም እኮ ተለየኝ። በእርግጥ ሰዎችም ስለተለየኝ ራሴን የጣልኩ ይመስላቸዋል፤ ስልኩን ስለማያነሳልኝ ዱካክ እየበላ የሚያሰቃየኝ ነው የሚመስላቸው፤ ከእኔ መሸሹ ብቻ የመቆም ድፍረቴን የናጠው ነው የሚመስላቸው።

ግን አይደለም!

ሁሉን ነገር ተራ ማድረጉ አስደንግጦኝ ነው! አብረን ሳለን ያልወጣንበት የሐሳብ መሥመር፤ ያልተንሸራሸርንበት ስፍራ፤ ያልነገርኩት ገመና አልነበረም፤ ያልሆንነው አለመሆንን ብቻ ነበር!!





በየደቂቃው ከጭንቅላቴ የሚፈልቀውን ዝባዝንኬ ሳላስቀር፣ በአጠገቤ ውል ያለውን ሳይቀር ነበር የምተነፍስለት። እንዳልቆም አድርጎ ያፍረከረከኝ፤ ያሳለፍነውን፣ ያገዘፍኩትን ነገር አንድ ሳይቀር ነው አሳንሷት የሄደው። ትረካ የሌለው መለያየት፣ ውጣ ውረድ የሌለው ፍቺ፣ የማይተነፈስ ሕመም ለማይታይ ጠባሳ ይዳርጋል። እንዴት በዚህ መጠን ተራ ይሆናል? እንዴት እየተፍለቀለቅሁ የምተርከውን ትዝታዬን እንደዚህ ያባከነዋል?

እንዴት ጥሩ ምክንያት አይፈበርክም?

እንዴት አካሄዱን ወዝ አያላብሰውም?

በዚህ መጠን ተራ አድርጎኝ እንዴት ይሄዳል? ያውቅ የለ ማን እንዳሳደገኝ፤ ለክብሬ ለግንኙነታችን ያለኝን ቦታ እያወቀ።

እችን ብቻ ነበር የምናከለው?

አብረን ስንሆን የእኔ ነው ብዬ አይደል እርቃኔን የተንጎማለልኩት?

የነበረን ነገር ቢያይል አይደለ ድክመት እና ስጋቴን መግለጼ?

ያሳለፍነውን ውብ ጊዜያት ካለጥንቃቄ በአካሄዱ ተረማምዶበት ነው ያናወዘኝ፣ እንጂ'ማ መለያየት ተፈጥሯዊም አይደል? ነፍስስ ከስጋ ይለይ የለ? መሄዱ አይደለም፣ አካሄዱ ነው መላቅጡ የጠፋ ዱካክ ውስጥ የዘፈቀኝ።

አወዳደቃችን ውስጥ የጣያችን ግዝፈት እና ተራነት አሻራ በጉልህ አለ። ምን አለ አለሳልሶ ቢጥለኝ? ምን አለ ሲተወኝ ይሉኝታ



Scanned with CamScanner

ቢስ ባይሆን። አብረን በነበረን ጊዜ እንደምወደው እያንዳንዱ ዳናዬ ምስክር ነበር። ሰው ለሚወደው አይደለም ላሸነፈው ጠላቱ እንኳ ይራራ የለ?

ምን አለ ራርቶልኝ ቢሆን...

ምን አልባት እኮ የእኔ ብቻዬን የመሆን ፍርሀት ሲያርደኝ መለማመጤን አይቶ ነው ለእኔ ያለው ስሜቱ የተከለለበት፤ ምን አልባት ከእኔ የተሻለ ሰው አግኝቶ በእጁ እስኪያረጋት ወረት አውሮት ነው።

ምን አልባት እንዲህ መሙለጭለጭ ማንነቱ ይሆን ይሆናል።

እሱ እንዳልሄድበት ከመጣው መንገድ በላይ እኔስ አልሄድኩም? ለእናቴስ የጀመርኩትን የደበቅኋት፣ የማትወደውን የሆንኩት ነገ ስነግራት አታፍርብኝም ብዬ አይደል? ከራስ ሰው ጋ መንዘላዘል ትዝታውም ሁኔታውም ይጣፍጣል ብዬ አይደል ከእናቴ የዘወትር ስጋት ራሴን ጥዬ ያገኘሁት?

ይሂድ! መሄዱ አይደለም ያጎሳቆለኝ!

ይሄ ማለቂያ የሌለው የምን አልባት ጉዞ ነው ከሰውነት ተራ ያወጣኝ። ምን አልባት ቃል ገድፌ የማይወደውን ብዬ፣ ወይ ምን አልባት ያልዋልኩበትን ነግረውት ይሆን? ወይ የሆንኩትን አገዛዝፈው አሻከረውት ይሆን? ይሄ እና ሌሎች የምን አልባት መላምቴ ነው ጭንቅላቴን ያጣበበው፤ እንዲህ እንደባተልኩ አልቀርም፤ አረሳዋለሁ። ያኔ እዚህ የዘራውን እዛ ሲያጭድ መሰስ እያለ ይመጣል፤ ያኔ የእኔን የምን አልባት የመላምት ችንካርን ይቀምሰዋል።"





ተሾመ ረጋ ብሎ ነበር የሚመለከተኝ። ሶልያና ያለችውን ሳነብ አንዱም ቃል አልለሰለሰኝም። ልቤን የጥፋተኝነት ስሜት ሸቀሸቀኝ። እያነበብኩ እንባዬ ሲንከባለል ተሾመ ተረጋግቶ ከመቀመጥ በቀር ምንም አላደረገም። ስቃይህ ከስቃይዋ አይበልጥም ብሎ ይሆናል።

ሶልያና ሕመሟን ከመቼ ጀምሮ ነው እንዲህ ለሰው ማጋራት የጀመረችው? አንዳንድ በደል የሌለንን ማንነት እና ባሕሪ ይወልዳል ማለት ነው።

አለሌ ብሆንም ስንቴ እየወደድኩ ተትቻለሁ፤ እየለመንኩ ተረግጫለሁ፤ ከእኔ የተሻለ ጋ ሄዳለች ብዬ ናፍቆቴን ፊት ነስቻለሁ። ጭር ያለ ስፍራ ተሸጉጬ አልቅሻለሁ። በሌላ አሳብቤ ተነጫንጫለሁ። ስንት ጓደኛ ሸምግልና ልኬያለሁ፤ የኔ ያድርጋት ብዬ ጸልያለሁ፤ አለመፈለጌን ለመርታት አነቃቂ ንግግር ሰምቻለሁ፤ ሴት እንዲህ ነች ብዬ ተቦትርፌያለሁ። ጥላኝ ማን ጋ እንደሄደች እያሰብኩ አርሬያለሁ።

ቃሏን እያጣቀስኩ ከስሻለሁ፤ ናፍቄ ረግሜያታለሁ። ይሄ እንዲህ ሆኖ ሳለ የሚወዱትን በገዛ ፍቃድ እንደመተው ያለ ሕመም ግን የትም የለም!

# ሰወርደ ሲዋረድ

የድሪባ ጓደኞች ቤት ሲመጡ፣ መንገድ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያገኙኝ፤ ከእኔ ጋ የተማሩ ሲጠሩኝ ቤት ሲመጡ አልያም መንገድ ላይ ድሪባን ሲያገኙት የሚደነቁበት ነገር ቢኖር መንታ መምሰላችን ነው።

ሁለታችንም ረጅም፣ ሁለታችንም ጥቁር፣ ሁለታችንም ሌንጮጫም፣ ሁለታችንም ትላልቅ ነጭ ድርድር ጥርስ ያለን፣ ሉጫ ጥቅጥቅ ባለ ጸጉር መሀል አናታችን ላይ ብን ያለች አመድማ ጸጉር (በእርግጥ የእሱ ጸጉር ሸብቷል፤ የቀኝ ጆሮችን ጫፍ ቁልምም ያለች፣ ወፍራም ደፍጠጥ ያለ አፍንጫ፣ ጎላ ያሉ አይኖች ያለን፤ በአጠቃላይ በዕድሜ የምንለያይ መንታዎች ነው የምንመስለው። አብሮን የኖረም ለአፍታ ውልብ ስንል ላየንም አባት እና ልጅ መሆናችን ያለ እማኝ ያውቀዋል። ያየን ሁሉ ጥጋበኝነታችንን የሚረዳ፤ ብዙ የማናወራ፤ የችግር መፍቻ ቁልፉ ዱላ የሚመስለን፤ ሁለታችንም ምቹ ፍጡሮች አይደለንም።

ከእኔ በስተቀር ሦስቱም ሴት ልጆቹ ውድነሽን ነው የሚመስሉት። እሷ ልዩ ነች እንጂ፤ በባሕሪም ትንሽ ይመሳሰሏታል። ውድነሽ ግን ምን ይሁን ብላ ይሆን ድሪባን ያገባቸው?





ዓለም ላይ ከሚደብረኝ ነገር ማስቀየሜ፣ ሌንጮጫም፣ ድፍጥጥ፣ ለአደን የተዘጋጀ ነፍሰ ገዳይ መምሰሌ አይደለም። ድሪባን መምሰሌ እንጂ!!

እኔ የቤቱ ብቸኛ ወንድ እና የመጨረሻ ልጅ ነኝ። ዝምተኛ የሆንኩት በሴቶች ጫጫታ ውስጥ ስላደግኩ ይሆን ወይም እህቶቼ እየተቀባበሉ ስለሚያወሩ ዕድል ነፍገውኝ ይሆን፣ ድሪባን በባሕሪ ስለምመስል ይሆን አላውቅም ብቻ ለዱዳ የቀረብኩ ዝምተኛ ነኝ!!

ድሪባ ካለ እህቶቼ እንደልባቸው አይቅለበለቡም፣ ይንሾካሾካሉ። የድሪባ መኖር ምቾት አይሰጥም መሰለኝ የቤቱ ሁኔታ እሱ ካለ እና ከሌለ ይለያያል። እንዴት ሰው አንድ ቤት ውስጥ እየኖረ አይደፋፈርም? እንዴት አይለመድም? በእርግጥ ድሪባ እንዳይለመድ የሚያደርገው የጎረበጠውን ነገር በዱላ ለማስተካከል ስለሚሞክር ነው። ሲማታ ደግሞ ከዱላው ሁኔታው የበለጠ ያስፈራል፤ ሚስቱ ውድነሽ ሳትቀር ትፈራዋለች።

እኔ

ዓለም ላይ ብቸኛው የማልደራደርባት፣ የማልናደድባት ፍጡር ውድነሽ ነች። ዓለም ላይ የእኔን ያህል የሚቆረቆርላት የሌለ የሚመስለኝ፤ ውጪ ቆይቼ ናፍቃኝ አይኗን ማየት የሚርበኝ ውድነሽ ብቻ ነች። ውድነሽ እናቴ።

በእርግጥ ፍቅሬን ነግሪያት አላውቅም። የሚሰማኝን መናገር የማልችል ፍጡር ነኝ። የምወዳትን እናቴን እንኳን ለማቆላመጥ የማልችል ሰው ነኝ። ውድዬ ብዬ ለመጥራት ተለማምጄ ፊቷ ስደርስ



Scanned with CamScanner

ድንጋይ እንደጎረሰ ሰው ምላሴን ማንቀሳቀስ ይሳነኛል። በርግጥ እንደምወዳት አይጠፋትም። የምንወዳቸው ፍቅራችንን ለመረዳት ቃል አያስፈልጋቸውም።

ለኔም ምድር ላይ የምታዝንልኝ ውድነሽ ብቻ ነች። ሌላው ግዝፈቴ፣ ጥጋቤ፣ ልበሙሉነቴ እና መልከ-ጥፉነቴ ነው የሚታየው። ውድነሽ እንኳን ለእኔ ለልጇ እንደ ልጆቹ በጩኸት ለሚያስበረግጋት ድሪባም ጭምር ታዝናለች።

ልጅ እያለሁ ሲመታት ሴቶቹ ይጮሃሉ፣ ያለቅሳሉ፣ ይለምኑታል፤ እኔ ብቻ ነኝ ለማስለቀቅ አንዴ እግሩን አንዴ እጁን በመያዝ ለማስጣል የምሞክረው።

አንድ ቀን ግን ሲያንቃት ጀርባው ላይ ዘልዬ ወጣሁበት!!!

እናቴን ለቆ በብርሃን ፍጥነት እጄን ልኮ ከጀርባው በፈርጣማ ክንዱ ካላቀቀ በኋላ አየር ላይ አንጠልጥሎ፣ መሬት ሳያወርድ አርገፍግፎ ያልተነሳው ፍራሽ ላይ አሽቀንጥሮ ወረወረኝ። እናት እና እህቶቼ እሪሪ አሉ። ገደለው... ገደለው... ገደለው ሲሉ ጎረቤቶቻችን እሪታ ሰምተው እንደተለመደው ለምነው አስጣሉኝ።

እህቶቼ የተጎዳሁ መስሏቸው ነበር። እኔ ግን ከንፈሬን ነክሼ፣ ፊቴን አጨማትሬ ደግሞ ውድነሽን ከያዛት ልታገለው ራሴን እያዘጋጀሁ ነበር። "አንተ ሴጣን ነግሬሃለሁ በእጄ እንዳትጠፋ" ይላል። ከሁለት ቀን በኋላ ሁሉም የቤቱ አባል የድሪባን ብልግና ይረሱለታል፤ ከእኔ በቀር!





ድሪባ አምባገነን ነው። አጥፍቼ ተናዶብኝ፣ ስሞታ መጥቶበት ሲመታኝ ቃል አልተነፍስም፤ ዱላውን አንገቴን ደፍቼ በጥሞና እቀበላለሁ። በእርግጥ የሚፈስ ዓይነት እንባ የተሰራልኝ አይመስለኝም። በጣም ካመመኝ፣ ከተናደድኩ አልያም ካዘንኩ አይኔ እንባ ያረግዛል፣ በጣም ወረደ ቢባል ሽፋሽፍቴን ከማራስ አይዘልም!!

ድሪባ ውድነሽን ከነካት ብቻ ነው የማልፈራው፣ የምደፍረው፣ እየወረወረኝ ተነስቼ ተዋት ዓይነት እግሩን፣ እጁን፣ ልብሱን ለመያዝ የምታገለው።

ውድነሽን እንደምወዳት የሚገባኝ ያን የሚያክል ሰውዬ ለመታገል ስፍጨረጨር ነው። ስንቴ እያነሳ ሲያፈርጠኝ፣ ሲጠምደኝ፣ ሲጠላኝ፣ ሲፎክርብኝ ውሎ ቢያድር ውድነሽን ሲጮህባት ፊቴ ይቀያየራል። ሲመታት ሲነሳ ላገላግል፣ ላስጥላት ብድግ እላለሁ። እህቶቼን ሲመታቸው፣ ሲቆጣቸው ቀናም አልል፤ እኔ ግዴታዬ፣ ፍቅሬ፣ ኃላፊነቴ ውድነሽ ጋ ብቻ ነው። ከሚያምንበት መንገድ ዝንፍ ያለ ካለ፣ አታድርጉ ያለው ከተደረገ፣ ጥያቄው በአግባቡ ካልተሰማ፣ ለውድነሽ ትዕዛዝ ተገቢ ያልሆነ ምላሽ ከተሰጠ፣ ያልሆነ ነገር ከሰማ በአይኑ፣ በሌባ ጣቱ ይፎክራል። መፈራት አይሰለቸውም፤ እንዲህም ሆኖ ግን እህቶቼ ይወዱታል፣ እሱን ለማስደሰት ሽር ጉድ ይላሉ።

ስፖርት እወዳለሁ። ከትምህርት የተረፈኝን ጊዜ ሰውነቴን በማጠብደል ነው የማሳልፈው። አብረውኝ የሚማሩት ተማሪዎች እና አንዳንድ አስተማሪዎቼም ጭምር ራምቦ ይሉኛል።



Scanned with CamScanner

ቤታችን ውስጥ የወታደር ፎቶ የለበሰ የድሪባን ፎቶ እያየሁ ስላደግኩ ወታደር አልወድም። ያው እኛ ቤት የመጨረሻው ስልጣን የድሪባ ነው። ሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈጻሚው፣ ሕግ ተርጓሚው እሱ ነው። ሌሎቻችን ሕዝብ ነን፣ ድርሻ የለንም፤ ድርሻችን እሱ በፈለገው መንገድ መጓዝ ብቻ ነው።

ጭቆና ስለማልወድ ይሆን፣ እንደ ድሪባ ጥጋበኛ ስለሆንኩ ይሆን፣ ውድነሽን ስለሚጨቁናት ይሆን እንደ እሱ አምባገነን ስለሆንኩ ይሆን ብቻ ድሪባ ምቾት አይሰጠኝም። አግብቼ እስከወጣ ድረስ እንደተፈራራን፣ እሱም ውድነሽ ላይ መነሳቱን ሳይተው እኔም መከላከሌን ሳላቆም አግብቼ ከቤት ወጣሁ።

አንድ ዕለት ልትወልድ ቀናት ለቀራት ሚስቴ ያራስ እህል ውሰድ ብላ ጠርታኝ፣ አድካሚ የሥራ ውሎ አሳልፌ፣ ከአለቃዬ ጋር ያደረግሁትን ንትርክ ለመርሳት ከጓደኞቼ ጋር ትንሽ ቀማምሼ አራት ሰዓት ሰፈር ስደርስ፣ ሰፈራችን በሰው ተጨናንቋል። የግቢያችን መግቢያ፣ ግቢያችን ውስጥም በመንደሩ አዛኝ፣ ወረኛ፣ ታዛቢ፣ አሽሟጣጭ፣ ውሪ ሕፃናት ተከቦ ነበር። ይሄ ሰውዬ አሁንም ባሕሪው አልለቀቀውም።

የሆነውን ለማወቅ በደመ-ነፍስ ወደ ቤታችን መወርወር በሚመስል ሁኔታ ገባሁ። ድሪባ ውድነሽን አንቆ ይፎክራል፤ የመንደሩ ሰዎች እንደ ድሮ ይለምኑታል። በደመ-ነፍስ የሚለምኑትን ሰዎች ገፍትሬ አነቅኹት። ወደ ሌላ ግድግዳ ጠርዝ የለበሰውን ግራጫ ትልቅ ሹራብ በሁለት እጄ ጨምድጄ ወሰድኩት።





ድሪባ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈራኝ አየሁት። ድሪባ ጊዜ እንደተካው ለመጀመርያ ጊዜ ያወቀ ይመስለኛል። ትናንት ዛሬ እንዳልሆነ የማይረዱ ሰዎች ናቸው ከነክብራቸው የማይሞቱት።

እናቴ ከአትጉዳኝ ልመና ወደ አትጉዳው ልመና ከመቼው እንደተሸጋገረች አልገባኝም። እግሬ ላይ ወድቃ "ልጄ ልጄ አመል ሆኖበት ነው እንጂ እኮ አይጎዳኝም፤ ለመጉዳት ቢፈልግ ሰው ሳይሰበሰብ፣ ሳልጮህ አይጎዳኝም ነበር። ልጄ ልጄ ሮብሰኔ ... መከታዬ" እያለች አለቀሰች። ድሪባ እንደ እሷ መለመን ስለማይችል በፊቱ ማረኝ ያለ ይመስለኛል፤ ልገለው እንደሆነ አልተጠራጠረም መሰለኝ።

"እኔን... ሮብሰን... እኔ...ን?" አለኝ ተማጽኖና ተሃዝቦት የተላበሰ ፊት እያሳየኝ።

ውድነሽን ሲነካብኝ በልጅነት አጥንቴ ሳይጠነክር፣ ትከሻዬ ሳይሰፋ፣ አካሌ ሳይጎለማ ለመታገል እንደተዘጋጀሁ እረሳው። እግዜር ሊበቀለው የራሱን ፊት እንደሰጠኝ፣ የራሱን ጥጋብ እንዳወረሰኝ አልተገለጠለትም ነበር። እግዜር ሲቀጣ ሂደቱን የውጤቱ ቀን ነው የሚገልጸው።

ያነቅኩበትን አንዱን እጄን ለቅቄ፣ እጄን ጨብጬ በኃይል አራት ጊዜ ያህል ደጋግሜ ሰነዘርኩ። ቤቱ ተንቀጠቀጠ፣ እናቴ ጮኸች፣ ቤት ውስጥ የነበረው ሰው ሊይዘኝ ስለፈራ ለመነኝ...

በአርግጥ ቡጢዬን ያሳረፍኩት ከፊቱ ጎን ያለው ግድግዳ ላይ ነው፤ ግድግዳው ተሰነጣጠቀ፤ ግዝፈቴ ይሆን፤ ብስጭቴ ይሆን፤ ግድግዳችን ስለማይረባ ይሆን አላውቅም!!

"ተው ልጄ ተው" አለኝ...

ድሪባ ለካ መለመን ይችላል፡፡ ወይም ዕድሜ ሲገፋ፣ አቅሙ ሲደክም ልመና ለምዷል፤ መኖር ለካ ብዙ መገለጫችን ያልሆነ ነገር ጨምሮ ያስለምዳል፡፡

የተሰማኝን ማውራት ብችል ኖሮ - ምን ታድርግህ? ምን አድርጊ ነው የምትላት? ዕድሜ አያስተምርህም? አይበቃህም? እለው ነበር፡፡ ማድረግ የቻልኩት ሽፋሽፍቴ ላይ የተሞጀረ እንባ ማሳየት ብቻ ነበር!!

ስላልታደለ እንጂ አውሬው ልጁ እሱን ነበር ሊከላከለው የሚገባው፤ ስላልታደልኩ እንጂ ያሳደገኝን ሰውዬ እንደጠላቴ አልቆጥረውም ነበር፡፡

ለቀቅሁት... ለመጀመሪያ ጊዜ መግዘፌ አስጠላኝ፡፡ ትናንት አቅም አልባ እያለሁ እናቴን ለማዳን ስፍጨረጨር የነበረው ስሜት ይሻል ነበር፡፡ ፍቅር ማለት ለሚያፈቅሩት ሲሉ ከማይችሉት ጋ መታገል እንጂ የሚያሸንፉትን ማሸማቀቅ አይደለም፡፡ ስለቀው እንባው እንደ እኔ ሽፋሽፍቱ አልገደበውም አለቀሰ፡፡ ያ ሞገሳሙ ድሪባ፣ በድምጹ የሚያርበደብደው፣ ተነሳበት የሚባለው፣ የሚለመነው፣ የሚለምኑት ጎረቤቶች ፊት ሲለመንለት ጊዜ አለቀሰ፡፡

ለካ አርጅቷል፣ ለካ አቅሙ እየከዳው ነበር፣ ለካ ማስበርገግ ሱስ ሆኖበት ነው፡፡ መለመን ምን ምን እንደሚል፤ መበርገግ በገዛ ልጁ





ምን እንደሚመስል በጎፈነነ ስሜት ውስጥ ሆኖ አየው፡፡ ድሪባ ሲያለቅስ ሳየው ዘመናት ሙሉ ከሽፋሽፍቱ ወርዶ የማያውቀው እንባዬ ጉንጩ ላይ ሲሄድ ታወቀኝ፡፡ ለምን ይሄን ያህል እስኪያለቅስ አሳዘኜው፣ ተፈታትኜው አንቄው ሳለ ሽጉጡን አውጥቶ ካልገደልኩት ብሎ አልተገለገለም፡፡

ቲሽ!!!

ውድነሽን ባይነካብኝ ኖሮ መቼ አዋርደው ነበር? ደግሞስ ምን አገባኝ ሚስቱ አይደለች? ደግሞ ሲያመው ትደነግጥ የለ፤ ሲያማት የእኔን ያህል መጨነቁ ይታይ የለ፡፡

እሷስ መቼ እንደምትጠላው ስታወራ ሰምቼ አውቃለሁ? መቼ ስለጥፋቱ ለልጆቿ ሆነ ለሌላ ስታወራ መቼ ሰማሁ? መቼ አጣጥላው አይቻት አውቃለሁ... መቼ??!

ከድሪባ ጋር በጸባይ የምንመሳሰል መስሎኝ ነበር፡፡ እውነቱ ግን እኔ አውሬ ነኝ!!

እንባዬ በጉንጬ እየወረደ ስልኬ ጠራ፡፡ የሚስቴ እናት ናቸው፡፡ አንስቼ ሄሎ ስል ከእልልታ መሀል "ሮብሰን የወንድ ልጅ አባት ሆነሀል፡፡ መልኩ ደግሞ ቁርጥ አንተን፡፡ መንታ ነው ምትመስሉት" አለችኝ፡፡



Scanned with CamScanner

# እንባ አደሽ ነፍሶች

አብረውኝ ከሚሰሩት ለየት ይልብኛል፤ ግሬይ፣ አመድማ፣ ሽሮ ከለር ልብሶች ያዘወትራል። አይዘንጥም፣ ጸጉሩን ስለማይንከባከብ የብርድልብስ ብናኝ በተለይ ጠዋት ላይ ከጸጉሩ አይጠፉም።

ጺሙን በቶሎ አያነሳውም፣ ከሰው ጋ አይተራረብም፣ ሰው ሲተረብም አይስቅም። ፖለቲካ ይከታተላል፣ አንባቢ ነው፤ ቅዱስ ዮሃንስ አፈወርቅን ይወደዋል፤ ጆን ሎክን ይተነትናል፤ አረቄ ነፍሱ ነው።

አንዳንድ ጠዋት የተመሳቀለ ፊት ይዞ ይመጣል። ፊቱ አልኮል ያመሳቀለው ይመስለኛል። ስለ ራሱ አያብራራም፣ ሰው እሱ ላይ ስለሚይዘው አቋም አይጨንቀውም። የሚረዳው የለም ብዬ ዋስ ጠበቃ ለመሆን እጋጋጣለሁ፣ ግን ነገሮችን ስለሚመረምር ለራሱ አያንስም።

ሲያወራ፣ ሲሰማ፣ ሐሳብ ሲሰጥ ጥድፍ ጥድፍ አይልም። የዋዛ እንቅስቃሴዎቹ ላይ እንኳን አስተውሎትን እመለከታለሁ።

ሰኞ ዕለት ያሳደገው፣ ያስተማረው አንድ ወንድሙ በመኪና አደጋ ሞተበት። የቢሮ ሰዎች ተሰባስበን ቀብር ላይ ተገኘን። ብሩክ ፍልስፍናው፣ መጀናተሉ ቀሰስ ማለቱ ከእሱ በኖ ጠፉ። መሬት





እየተንከባለለ ሲያለቅስ ሳየው አንጀቴ ተንሰፈሰፈ። እንባዬ አካላቴን ሳላወናጭፍ፣ ድምጽ ሳላወጣ ወለል እያለ ወረደ። ብሩክ አቅም አልባነት ሲያጥመለምለው፣ ለብዙ ሰው አለኝታ የነበረውም ወንድሙ ተጀቡኖ ወደ ጉድጓድ ሲወረወር ከንቱነት በላኝ።

በነጋታው ጠዋት ከእነ ዱካኬ ከእንቅልፌ ነቃሁ። ተጣጥቤ፣ ቁርሴን በልቼ ከሥራ መልስ ብሩክ ጋ ለመሄድ ጥቁር ሻርፔን ቦርሳዬ ውስጥ ከትቼ ወደ ቢሮዬ ሄድኩ።

አይኔን አላመንኩትም፤ ብሩክ ወንበሩ ላይ ፋይል ከምሮ አንገቱን ደፍቶ ይሠራል። ሳየው ደነገጥኩ፤ በደመ-ነፍሴ ብሩኬ ስለው ኮስተር እንዳለ በማያቀርብ አስተያየት እያየኝ "ሰላም ሊዲያ" አለኝ።

ሁላችንንም ፊት ነሳን። በሌሊት ሥራ ይገባል፣ አምሽቶ ይወጣል፣ ምሳ ብቻውን ይበላል። አይኑ አባብጦ እንባ ያሸበረው ፊት አይበታለሁ፤ ማንም እንዳያጽናናው መንገዱን ዘጋጋው። አለቃችን እንኳን በረታህ ብሎ ሲጀምር አዎ ይልና ከአጠገቡ እብስ ይላል፣ ወይ ደግሞ ወሬ ይቀይራል።

ወንድሙ ካለፈ በአስራ አራተኛው ቀን ላይ ብሩኬ ደህና ነህ? ግን ምነው እራቅከኝ? አልኩት።

"ትንሽ ቀን ነው የምፈልገው ደህና እሆናለሁ፤ ሁሉም ደህና ይሆናል" ብሎኝ ጭጭ አለ።



Scanned with CamScanner

በቅጡ አንዳላጽናናህ እኮ መንገዱን ዘጋኸው፤ ሰው በሚያስፈልግህ ጊዜ ነው ከሰው የራቅከው አልኩት። አየኝ፣ አጎነበሰ ቀስ ብሎ ቀና ብሎ እያየኝ ከትንሽ ዝምታ በኋላ...

"ይሄውልሽ ሊዱ ማጽናኛችን የጎደፈ ነው፤ አንዳንዱ ቤትሽ የሚመጣው ለወጉ ነው፤ አይኑ ላይ ምንም እንባ ሳይታይ ወንድሜ፣ ወንድሜ እያለ ድንኳን ውስጥ ይገባል። አጠገብሽ ይመጣና ምን አገኘው? ገጪው ተያዘ? ወንድሜ፣ ሰላምተኛዬ፣ ጥሩ ሰው፣ መከታዬ ይላል። ሐኪም ቤት አልወሰዳችሁትም? ጥያቄ በጥያቄ። የሚያስቆጭ፣ ሐዘን የሚፈጥር ጥያቄ፣ እጦቴን የሚያጎላ ጥያቄ። እንዳልታዘበው፣ እንዳልቀየመው ሐዘንህን መጥቻለሁ ፊቶች፣ ፊታቸውን ለማሳየት የሚጋጋጡ ሰዎችን ጋቢ ለብሶ መታዘብ ሕመም ነው።

በጣም ከባድ ነው ሊዱ፤ ሁሉም የሚጽናናበት መንገድ ሊሆን ይችላል እኔ ግን አልቻልኩም፤ የአጽናኞቼን መንገድ የዘጋጋሁት ሆን ብዬ ነው። ለማጽናናት ስለጉዳዩ ማተት የግድ አይደለም እኮ፤ አብሮ መሆን በቂ ነው፤ ማቀፍ በቂ ነው። ጊዜ ኃያል ነው፤ የማያዶለዱመው ሕመም የለም።

ወንድሜ ጋሼዬ ለእኔ ብዙ ነበር። እሱ ነው ያሳደገኝ፤ የምምለው እንኳን በእሱ አይደል? ለቁም ነገር እንድደርስ ያልሆነልኝ አልነበረም፤ ኃላፊነቱ ነበርኩ፤ የበኩር ልጄ ነው የሚለኝን ወንድሜን ነው ያጣሁት። ጉዳዩ ከእግዜር ጋ ነው።





እሱ ነው የተመሳቀለውን እጦቴን በመልክ በመልኩ በእግዜርኛ የሚያበጃጅልኝ፤ እንጂ'ማ በፍጡር ሊያውም ማብሸቅ በሚመስል ማጽናኛ አልድንም። ለዚህ ነው ከቀብር ጀምሮ ቤተክርስትያን የማድረው። ከአማኝ ጥቅማጥቅማችን አንደኛው ከአቅማችን በላይ የሆነ ሁነት ሲጋረጥብን እግዜር ላይ ሙጥኝ ማለት አይደል? ከትናንት ዛሬ በደንብ እየበረታሁ ነው፤ የታመንኩት አምላክ እያጽናናኝ እያጸናኝም ነው።"

የብሩኬ አወራር፣ ሁኔታው፣ ሕመሙ አንጀቴን አላወሰው። አይኔ ላይ ያቀረረው እንባ አለመውረድ አልቻለም። አንድ ነገር ብቻ አልኩት

እግዜር ያበርታህ ወዳጄ።

# አርፋጅ

አንድ ሰፈር ነው ያደግነው። አንድ ዩኒቨርስቲ ተማርን። ብሩክ ፈታ ያለ ነው፣ ጨዋታ ያደምቃል፣ ጨዋታም ያውቃል። እሱ ካለ የሳቅ ድምጽ አይጠፋም። ስድስተኛ ክፍል አልፈልግህም ተብሎ የተላከለትን ደብዳቤ አባቱ አግኝቶበት የመታውን ጠረባ፣ 'ለፍቺም ደርሰህልኛላ' እያለ የሚጠልበውን ጡለባዎችን እየቀመመ ሲያጫውት አፉን ከፍቶ የማይስቅ አልነበረም።

ታላቅ ወንድሙ ላይ የሚሠራውን ተንኮል፣ የግድያ ሙከራ የሚመስሉ ድብደባዎችን ኮስተር ብሎ በፌዛም ፊቱ እያወጋ ያዝናናን ነበር። ግሬድ ሲሰቅልም፣ ሲሾቅም ማላገጡ የሚጠበቅ ነው። በዙሪያው የማንጠፋው ፍሬንዶቹ ላይ እንዳይደብረን አድርጎ ለጨዋታ 'ፐርፐዝ' ብቻ ይቀልድብናል።

ብሩክ እንደ ጃካራንዳ ዛፍ በዙሪያው የሚያጅበው አይጠፋም፣ ሰው ይወደዋል። ከሰው ጋ አይጋጭም፣ መከባበር የማይደራደርበት ዋነኛ ፖሊሲው እንደሆነ በደንብ የሚቀርበው ሁሉ ያውቃል፣ የጠበቀ ወዳጅነት ያለን ደግሞ በይበልጥ እናውቃለን።

ብሩክ ለእኔ ወንድሜ ነው የማልለው ባልጀራነትን ማሳነስ ስለሚመስለኝ ነው። ብዙ ሳቅ እና ጭንቀቶችን ተጋርተናል። በድዬ ሳለሁ ለእኔ አግዞልኛል፣ እስከ ድከመቱ ተቀብየዋለሁ፤ ጓደኛዬ





ነው፣ ምንም ሳይኖረን ጊዜ ብቻ እያለን ነው ነፍሳችን የተናበበው፤ የጓደኝነት ትርጉም መተንተን ሳንጀምር ነው የተወዳጀነው።

እኔ ታላቅ ወንድሜ የጀመረውን 'ቢዝነስ' ተቀላቅዬ በሂደት ብዙ ሳንቲም ማግበስበስ ጀመርኩ። ብዙ ሀብት ባገኘሁ ቁጥር መፍጨርጨሬ ጠነከረ፣ ነገሮችን በውሎዬ ስለምመዝን እነጫነጫለሁ፣ ብሩክ ነገሮችን ከእሱ አንጻር ስለሚያይ መነጫነጩ አይገባውም።

ብሩክ ቀልደኝነቱ መፍዘዝ ጀመረና መገለጫው ያልሆነ ጨለምተኝነት ወረሰው። ምሬቱን ቀልቤን ሰብስቤ አሰላስዬ አላውቅም፣ መንገዱን ለመደልደል አልጣርኩም። ከእጮኛው ጋ የሚያጋጥመውን ግጭት በምሬት ሲነግረኝ ቀልቤን ሰብስቤ ከጊዜያዊ ስሜት የገዘፈ ይሆናል ብዬ አላሰብኩም።

የድሃ ልጅ መሆኑ፣ አይዞህ የሚለው አለመኖሩን ሲጠቅስ አብሬው ከማሽብሸብ የዘለለ ጊዜ ሰጥቸው ምን ላግዘው? ከእኔ ምን ይጠበቃል? ብዬ ለአፍታ አሰላስዬ አላውቅም።

እድገት ላይ በመመሰጤ ያሉኝን በረከቶች ለማስተዋል አልተቻለኝም ነበር። ያሉንን እየጣልን የምናመጣው አዲስ ስኬት እንደምን የምንፈልገውን ደስታ ሊያመጣልን ይቻለው ይሆን??

ለሥራ ኔትወርክ የማይሰራበት ቦታ ከርሜ ስመጣ እንድንጠጣ፣ እንድንስቅ ደወልኩለት ግን ስልኩ ዝግ ነው። ስልክ ማጥፋት፣ ደጋግሜ ደወልኩ፤ አሁንም ስልኩ ዝግ ነው።



Scanned with CamScanner

ስልክ አለማንሳት፣ ለብቻው መሆን አዲስ ያመጣው ፋሽኑ መሆን ጀምሯል። ቤቱ ልሄድ ተነሳሁ።

ፀሐዩ ሀሩር ነው፤ ዘንድሮ ፀሐዩን ለማምለጥ እንደዝናብ መጠለል እና መሮጥ መጀመራችን አይቀርም። የድሮ ሰፈሬ ደረስኩ፣ የነ ብሩኬ ደጅ ላይ ድንኳን ተደኩኗል፤ ብሩኬ አያቱ ጠንካራ ሕመም እያንገላታቸው እንደሆነ ነገሮኝ ነበር።

አያቱ በሕይወቱ ደማቅ ስፍራ አላቸው፤ ይወዳቸዋል። እንደ ወንድሙ ነበር የሚያዋራቸው፣ እንደ ጓደኛቸው ነበር የሚያጫውቱት። ከልጅነት ጀምሮ የምናቀውን ሰው ማጣት ሕመሙ ብርቱ ነው። ድብርት እና ምሬት ሳይጣባው አያቱ ሳይተኙ ለመድረስ ነበር የሚሮጠው።

እርምጃዬን ቀስ እያደረኩ ወደ ድንኳኑ ስሄድ የሰፈራችን ለቀስተኞች አይን እኔ ላይ አረፈ፣ አጎነበስኩ። ቀስ ብዬ የድንኳኑ መግቢያ በር ላይ ያገኘሁት ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ፣ በቀስታ ቀና ብዬ ብሩኬን በአይኔ ሳስሰው ወንበር ተደርድሮ በተቀመጠ ፍራሽ ላይ የደከሙ አያቱን አየኋቸው፤ ፍጥጥ ብዬ እንዳየኋቸው አስታውሳለሁ።

ከአጠገባቸው እናቱን አየኋት፣ በጥሩ መንፈስ አላየችኝም፤ አይኔ ወደ ተሰቀለው ፎቶ ተምዘገዘገ። ከዛ ሰዓት በኋላ የሆነውን ብዙ አላስታውስም። ለቀበሌ መታወቂያ ብሎ አብረን ሄደን የተነሳነው የብሩኬ ፎቶ ተሰቅሏል። በጣም እንደጮህኩ አስታውሳለሁ፤ እናቱን ሂሩቴን እየወደቅኩ፣ እየተነሳሁ የሆነውን





ለመጠየቅ ፍራሹ ጋ ለመሄድ መሞከሬንም አልረሳሁትም። የሆነውን ሁሉ አለማወቄ ተገለጸላቸው። ረጭ ያለው ለቅሶ ቤት ታወከ፤ ሁኔታዬ ያሳዘናቸው ሰዎች አብረውኝ ያለቀሱ ይመስለኛል።

አያቱን አንቄ ጋሽ በላይ ጓደኛዎት የት ሄደ፣ ብሩኬ የት ሄደ? አልኳቸው። በዛለ እጃቸው አቅፈውኝ በትኩስ እንባ ታጅበው እጁን በእጁ በላ አሉኝ። እግሬ አልጸና ያለ ይመስለኛል፤ ብዙ ሰዎች ያዙኝ፤ ከንዴን ከንዴን ብዬ ጮህኩኝ፤ ሰው ለካ እንዲህ ደካማ ነው፤ የቻልኩት መጮህ እና የሆነውን መካድ ነበር።

በቀን ብዛት ተበረታታሁ፤ ያወራነውን ሳሰላስለው ኋላ መቅረት ሲንጠው እንደነበር ገባኝ። ጨለምተኝነቱ ለመኖር ያለውን ፍላጎት ቀድሞ እንደገደለበት ገባኝ። ለካስ ማስተዋል አቅቶኝ ነው እንጂ ሁሉም ነገሩ ይገባ ነበር። አብረን ብንሆንም ለካ ተለያይተን ነበር፤ ለካ እሱ ነበር ጓደኛዬ እንጂ እኔ ጓደኛው አልነበርኩም። አናቱ ላይ በፍጥነት የወረረውን ሽበት ከ"stress"፤ ከሙብሰልሰል የተፈጠረ መሆኑን አልጠረጠርኩም ነበር።

ተሳከቶለታል የምባለው እኔ ነገሮች ሲጠሙብኝ፣ አንዳንድ ነገሮች ሲከፉብኝ ይቺ ዓለም እንደምትሰለቸኝ አውርቼው አላውቅም።

ራሴን ልገድለው እንደነበር ነግሬው አላውቅም። ሽራፊ ፈገግታ በሀሩር ፀሐይ ጤዛ እንደመፈለግ ሆኖብኝ ሳለ፣ የሞከርኩት ሙከራዎች ሲከሽፉ፣ ከሰው ሁሉ አነስኩኝ ስሜቴ ሲበላኝ፣ ብቻ

መሆን ሲጨፍርብኝ፣ አለመፈለግ ስሜት ሲወዘውዘኝ፣ ያለኝን ነገር ሁሉ ያፈሰስኩበት ተስፋዬ ሲጠፋ፣ ሕልሜ ሰፍቶኝ ስንከላወስ፣ የምሸሸግበት ጥግ ሳጣ፣ በማምነው ሰው ስካድ፣ ዕድለቢስነት እንዳልጠራጠር አድርጎ ሲመሰክርብኝ ራሴን ልገለው ዳድቶኝ ነበር። መዳዳቴን እንዴት ድል እንደነሳሁት ሳልነግረው!

አምላኬ ጋር ሙጥኝ እያልኩ፤

አንዳንዴ በረከቶቼን ፈልፍዬ ለራሴ እየተረኩ፤

አንዳንዴ ጭላንጭል ብርሃኔ ላይ ተመስጬ፣

ብሞት የምሰብራቸውን ሰዎች አዝኜላቸው።

አንዳንዴ ከቾች ያልኩበትን ጉዳይ እያላላሁ፣ አንዳንዴ ግትርነቴን እየገሰጽኩ፣ አንዳንዴ ሆስፒታል ያሉ አካላቸው የማይታዘዝላቸው ነፍሶችን እየረዳሁ፣ አንዳንዴ እስረኞችን እየጠየቅኩ ነው ራሴ ላይ የራራሁት — ሳልለው

ይሄ ትግሌ ለብሩኬ ትርጉም ሊሰጠው እንደሚችል ማሰብ አልተቻለኝም ነበር። የምንወዳቸውን ሰዎች ምን ያህል እንደምንወዳቸው ካለ እጦት እንዴት መረዳት ያቅተናል? ለራስ ሰው አለመድረስን ያህል አርፋጅነት የለም።



# ኀሰሳችን ከሽፎ እንጂ

ጥዑም ጊዜ ላይ ነበርን። ወይን እየተጎነጨን፣ እየተሳሳምን፣ ድንገት ሳላቅድ፣ ሳልቀምር፣ ሳላስብበት ከአንደበቴ የውስጤ እውነት አመለጠኝ።

ትክ ብዬ ሳያት ፈገግ ብላ "እችን የመሰለች ልጅ ጠበስክ አ?" አለችኝ ወደ ራሷ እያመለከተች፤ በትንሹ ፈገግ አልኩ። ፈገግታዬን እንደ መስማማት ቆጥራ በሚያምር ፈገግታዋ እያየችኝ "እናትህማ መርቀውሃል" ስትለኝ ይሄኔ ነበር የልቤ እውነት ያመለጠኝ።

ታውቂያለሽ ግን አንቺ ሕልሜ እንዳልሆንሽ፤ የመጣሽበት መንገድ፣ ዕቅድሽ፣ መርሕሽ ከእኔ ጋ መች ይሄዳል? አልኳት።

ሽማግሌ ከላኩሁኝ በኋላ፣ በጋራ ስለምንወልዳቸው ልጆቻችን ስናወራ ከርመን እንዴት እንዲህ ይባላል? ሁሉ እውነት እንዴት ይወራል? የልብ እውነት ሁሉ ይዘረዘራል?! ትበሳጫለች ብዬ ነበር ግን ደግሞ የጠበኩትን የፊት መለዋወጥ አላየሁም። ረጋ እንዳለች፣ ፊቷ ሳይለዋወጥ ትክ ብላ አየችኝ፤ ቅፍፍፍ የሚል ስሜት ዋጠኝ፤ ምን አለ አስማተኛ በሆንኩ እና እንዳልሰማች ማድረግ አልያም እንዳልተናገርኩ መሆን ብችል።

ቃላቱን እርግጥ አድርጋ

"ትክክል!! ጊዜው አሳዝኖን ነው አብረን የሆነው፤ አብረን ሆነን በስሱ ሌላ የፍለጋ ሙከራ ስላልተሳካልን ነው የምንጋባው። አንዲት ቀን 'Messenger'ህን ከፍቼ አይቻለሁ። የምታወራቸውን እንስቶች ቀልብ ለመግዛት የምትሄድባቸውን መንገዶች፣ መሻፈዶች፣ ላጤ ነኝ ጨዋታዎች፣ ብልግናዎች ተመልክቻለሁ፤ ሁሉም ከእኔ ጋ አንድ ዓይነት ነበሩ። የማደርገውን ነበር የምታደርገው፤ ከፍቶኝ ነበር እንዳላኮርፍ፣ እንዳልጨቀጭቅህ፣ እንዳልጣላህ ካንተ አለመሻሌ አሸማቀቀኝ። የብዙ ሰዎች ትዳር እንዲህ እንደሆነ አይቻለሁ፤ ከገቡ በኋላ በልጆቻቸው ይጽናናሉ፤ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሚስትና እና ባላቸውን እየከሰሱ ኑሮን ይገፉታል።

ለዛ ነው እንከን የለሽ ትዳር የሚያስሱት ቆመው የሚቀሩት! በቆዩ ቁጥር መለኪያቸውን እየቀየሩ ካጣጣሉት፣ ከተጠየፉት የኑሮ ቀንበር ላይ ራሳቸውን ያገኙታል። ለዛ ነው እንደሚታረድ በግ ሁሉን እያወቅኩ ሽማግሌ ስትልክ፣ ቀለበት ስታጠልቅልኝ፣ የልቤን እውነት አፍኜ የምከተልህ።"

ሲዘበራረቅብኝ ይታወቀኛል። ግራ ገባኝ፤ የሕይወት አጋርን በዚህ ደረጃ አለማወቅ ምን ይባላል? እችን ልጅ ነገሮች በዚህ ደረጃ ይገባታል ብዬ አላሰብኩም። ሴት ልጅ ትታለልልሃለች እንጂ አታታልላትም፤ እኔ እንዲህ እንደሚሰማኝ እንጂ እሷ እንደዚህ እንደሚሰማት አላውቅም ነበር።





ለምን ታድያ አብረን እንሆናለን ሁለታችንም እንዲህ ከተሰማን?

"እኔንጃ"

ምን አልባት ጊዜያችን፤

ምን አልባት ዕድሜያችን አሳዝኖን?

ምን አልባትም በዙሪያችን ያለ ውትወታ?

ምን አልባት ዘራችንን ለመተካት ካለን ፍላጎት?

ምን አልባት መላመዳችን እንዳንለያይ አግቶን ይሆን?

ምን አልባት አንዳችን ለአንዳችን ካለን ውስጣዊ ስሜት ይሆን?

ምን አልባት በዙሪያችን ካሉት ሰዎች የበለጠ ስለምንዋደድ??

ምን አልባት በስሱ ሌላ ለማግኘት ያሰስነው ኀሰሳ ስላልተሳካ??"

ሰው የልቡን ሁሉ አለማውጣቱ ይሆን ቁርኝታችንን ያላሳደፈው? ባለጋራችንን አለማወቅ ጠቀሜታ ይኖረው ይሆን? አንዳንድ ዕውቀት ምቾት አይሰጥም። ዕውቀት ትካዜን ታበዛለች እንዲል መጽሐፉ፤ አንዳንድ ውይይቶች ሸንቁር ያበጃሉ። የጀመርኩትን ወይኔን በአንድ ትንፋሽ ወደ ጉሮሮዬ አንቆረቆርኩት።



Scanned with CamScanner

እንደዚህ ዓይነት ሎጂክ ተዘባዝቦ - ግንኙነት፣ ትዳር መመሥረት ይቻል ይሆን? እንዳለችው ፍርሀት ነው? እጦት ነው? መላመድ ነው? ምንድን ይሆን በትክክል ያጋመደን?

ምን አስቸኮለን? ምን አሸበረን? ይሄን እውነታ ከተዘራዘሩ በኋላ እንዴት ጎጆ ይቀለሳል? ልጅ ሳይመጣ፣ ንብረት ሳናፈራ፣ ኑሮ ሳይንጠን የግንኙነታችንን መዓዘን መገምገም እንዳለብን ነው የገባኝ። አሁን የምጎዳት ነገ ከምሰብራት አይበልጥም፤ ዛሬ የሚሰማኝ ሕመም ነገ ከሚጋረጥብኝ መከራ አይበልጥም።

ማሬዋ ሰው ውድ ፍጡር ነው። ችኩላችን፣ ብልጣብልጥነታችን፣ በራሳችን ማስተዋል ላይ መንጠልጠላችን የእኛ የራሳችን የሆኑት ሰዎች ጋ አንድንሸዋወድ ያደርገናል። ጊዜ እንውሰድ፣ ተነጣጥለን ዙሪያችንን፣ መንገዳችንን እንመርምር፣ ብልግናችንን ይቅር እንበለው። የቆምንባቸውን ስፍራዎች እንቃኛቸው፣ ከፈጸምናቸው ጥፋቶች ጋ እንፋጠጥ፣ እናርማቸው፣ እናበጃጃቸው። ብቸኝነት አባብቶን፣ አቻ ግፊት ወትውቶን፣ መላመድ አሳስሮን፣ የቤተሰብ ግፊት ገፈታትሮን ኑሮ አይመሠረትም። የሁሉም ጓዳ እንዲህ ነው ተብሎ አዲስ ጎጆ አይበጅም፤ ሁሉም ሄዷል ተብሎ እንኳን በስሕተት መንገድ በትክከለኛ መንገድ መሄድ ተገቢ አይደለም።

ከመጣንበት መንገድ የምንሄድበት ሩቅ ነው። ራሳችንን ከእርስ በእርሳችን ነጣጥለን እናጢነው። የአስተውሎት መንገድ





ደግሞ አሜን ካልነው ባሻገር ያለውን እውነታ መጋፈጥን ይጨምራል።

ያኔ የውስጣችን እውነት ፍንትው ብሎ ይታየናል፤ ለውሳኔም ይረዳናል። ስሕተታችንን ለማረም ከፍርሀት ጋ መጋፈጥ የመጀመሪያው እርምጃ ነው።

ከዚህ ሁሉ መንገድ በኋላ መመለስ እንዳስፈራት ታስታውቃለች። እኔም የወጠንኩትን፣ የለመድኩትን፣ የወሰንኩትን ዳግም ለመመርመር እና ለመከለስ ሳስብ ደስስ የማይል የሚቀረዝዝ ስሜት ሲወረኝ እየተሰማኝ ነው።